# የኛ ብርቱካን

የኛ እንስት ጀግና የኛ ብርቱካን
ሳትቸር ሳትፈራ ጠብቃ ወገቧን
አሳየች መንገዱን ቀራጥነትን።
ለሰላማዊ ትግል የተዘጋጃችሁ
እራሷን ሰውታ ባረከችላችሁ
መንገዱን በርግዳ ከፈተችላችሁ
እንግዲህ አትፍሩ አለች ከጎናችሁ።
ታሰረች ቃሊቲ የኔ ብርቱካኔ
ለዕውነት ስልቀመች ቢከፋው ወያኔ
የኛን ብርቱካን የኛን ጽጌረዳ
ሰደዳት ቃሊቲ ለመከራ ፍዳ
ምንም ሳታጠፋ በመለስ ተፈርዳ።
አንድ ልጇን ጥላ ለህዝበ ኢትዮጵያ
ይህ ካልሆነ መቁረጥ ከወያኔ ፍልሚያ
ንገሩኝ ዕምታውቁ
ከወያኔ መንጋጋ የምትፈለቅቁ
አለያ አርፋችሁ ተቀመጡ
ወሬአችሁ ይቅር የባጥ የቆጡ።
ወይ አብራችሁ ቁሙ
ወይ ብቻ ቆዝሙ
እንደ ኢህአፓ መኢሶን
እራቅ ብላችሁ
አፋፍ ላይ ቆማችሁ
በስማ በላችሁ
በለው ማለታችሁ
ምን ሊፈይዳችሁ
ስምስ ማጥፋታችሁ
የናንተ ትግላችሁ በወሬአችሁ
ለወገን ሳይሆን ወገን ላይ መጮህችሁ።
ወይ ደሞ ልቀቁ
እንዲያው የጉራ ጦር አትሰበቁ
እንኳንስ ወያኔን እስከ ጥርሳቸው የታጠቁ
ቅጠልም አታነቃንቁ።

ከንፈ ሚካኤል
ታህሳስ ፴ቀን ፳፻፩ ዓ/ም